የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E   N E G A R I T   G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

፪^ኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
ድሬዳዋ የካቲት ፳፩ ቀን ፳፻፮

በትሬ□ኸ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd year No 33
Dire Dawa Feb 28 Day 2014

**አዋጅ ቁጥር ፴፫/፳፻፮**

**የድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ □ቃት አሰጣጥና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለማቋቋምና ተግባርና □ህላፊነቱን ለመ□ሰን □□□ አዥፀ ::**

በድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ□ □ቃት አሰ□ዓ ና ቁጥጥር አሠራር ራሱን ችሎ ያልተደራጀና በመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ ሥር በሥራ ሂደት ደረጃ ሆኖ ጥራት በጐደለው ሁኔታ□ □□ንባታ□ □ቃትና ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ሲያከናውን የቆየ በመሆኑ።

ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥንና ቁጥጥር የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም አደራጅቶ ለተገልጋዮች ፈጣን፣ ጥራት ያለውና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ::

**PROCLAMATION NO.33/2014**

**A PROCLAMATION TO ESTABLISH AND DETERMINE POWER AND DUTIES OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION CONSTRUCTION PERMIT AND CONTROL AUTHORITY**

Whereas; the issuance of construction permit and control activity of the Dire Dawa Administration were not organized independently and it deliver less quality service of construction permit and related activities as one core processor of land development and management Bureau;

Whereas; it has become necessary to organize an independent institutions which deliver quality, cost effective and expeditious services;.

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፩)«ሀ» በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ□ □ቃት አሰጣጥና ቁጥጥር ባለሥልጣን ለማቋቋምና ተግባርና ኃላፊነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር፴፫/፳፻፮›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. "አስተዳደር " ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፤

፪. <<ከተማ>> ማለት የድሬዳዋ ከተማ ነው።

፫. «ባለሥልጣን» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ□ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ነው::

፬. «የህንጻ ሹም» ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላ□ነት በዋናነት አን□ጸስ□□ም በአስተዳደሩ ካቢኔ □ተሾመ ሰው ነው::

፭. <<የምሽት ግንባታ>> ማለት ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሠዓት ባለው ጊዜ ውስጥ አዲስ ህንፃ መገንባት ወይም ነባር ህንፃን ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ማለት ነው።

Now therefore; in accordance with Article 12(1) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No 416/2004, the Dire Dawa Administration council, it is hereby proclaimed as follows

## Part one

## GENERAL

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as"a proclamation to establish and determine the power and duties of the Dire Dawa Administration construction permit and controll authority proclamation No33/2014

### 2. Definition

In this proclamation unless the context requires otherwise

1. "Administration" means Dire Dawa Administration
2. "city" means the Dire Dawa City
3. "Authority" means the Dire Dawa Administration construction permit and control authority which established in accordance with this proclamation.NO --2014
4. "Building officer" means a person who appointed by the Dire Dawa Administration mayor to implement the power and responsibility given to as per Article 9 of this proclamation
5. «Night construction» meаns the construction of a new bulding or the modification of an existing

building or alteraction of its use from 7:00 P.M-6:00 A.M /night time

6. Proclamation means Ethiopian building proclamation No 624/2009

፯. «አዋጅ» ማለት የኢትዮጵያ የህንፃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩ ነው።

፯. «ደንብ» ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የህንፃ ደንብ ቁጥር ፪፻፵፫/፪ሺ፫ ነው።

፰. <<ሰው>> ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

**<u>፫. የፆታ አገላለጽ</u>**

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

**<u>፬. መቋቋም</u>**

የድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ <<ባለስልጣኑ>> እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለውና ራሱን የቻለ የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**<u>፭.ተጠሪነት</u>**

የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለአስተዳደሩ ከንቲባ ይሆናል።

**<u>፮. ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የባለስልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በማዕከል ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም የከተማው ቀበሌ አስተዳደር ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የባለስልጣኑ ዓላማ፣ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር</u>

**<u>፯.ዓላማ</u>**

ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡:

7.“Regulation” means council of ministers build regulation No 243/2011.

8. “Person} means any natural or guridical person.

**<u>3. Gender Reference</u>**

Any eXpression in the masculine gender includes the feminine.

**<u>4. Establishments</u>**

The Dire Dawa Administration construction permit and control authority (here in after referred as” authority)“ is here by established as an autonomus organ of Administration government having its own legeal personality

**<u>5. Accountability</u>**

The authority shall be accountable to the mayor of the council of administration.

**<u>6.Head office</u>**

The authority shall have its head office at the center and may have branches at any kebeles of the Administration as may be necessary.

## <u>PART TWO</u>

## <u>Objective Organization and power and duties of the Authority</u>

**<u>7.Objective</u>**

The authority shall have the following objectives

፪. የመጠቀሚያና የማፍረሻ ፍቃድ ይሰጣል፣ የግንባታ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤

2. Control and following up building standard and provide to use and demolish permission thereof.

፫. አዲስ የግንባታ ፍቃድ፣ የምሽት የግንባታ ፍቃድና የአጥር ግንባታ ፍቃድ ይሰጣል፤

3. Provide new construction night construction and fence building Permission.

፬. ከግንባታ የሚወገድ ተረፈ ምርቶች መጣያ ፍቃድ፣ ጊዚያዊ የግንባታ ፍቃድ፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ ፍቃድ የነባር ግንባታዎች ማሻሻያ ፍቃድ፣ የእድሳት ፍቃድ እንዲሁም የማስታወቂያ ሠሌዳ ማቆሚያ ፍቃድ ይሰጣል፤

4. Provide construction wastage disposal, temporary construction, renovation and establishment, old amendment and Notice board establishment certificate.

፭. የፕላን ስምምነት አገልግሎት እንዲሁም መረጃና ማስረጃ ይሰጣል፤

5. Provide plan agreement services, information and evidence therof,

፮. የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማስረጃ ይሰጣል፤

6. Provide good performance certificate.

፯. የተፈቀደ ግንባታን በመሰረታዊ ካርታ ያመላክታል ዝርዝር መረጃውንም ይመዘግባል፣ የመጠቀሚያ ፍቃድ የተሰጣቸውን ግንባታዎች በመሰረታዊ ካርታ ያመላክታል፤

7. Indicate detail information licenced buildings and construction have use license on GIS.

፰. ግንባታ ቦታ በመሄድ ግንባታው ብቁ መሆኑን ያረጋግጣል፣ የግንባታ ግብዓት ጥራት ፍተሻ ያደርጋል፣ በግንባታ ወቅት የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ይፈታል፤

8. Ascertain and examine the quality of building and its input resolve disagreements happened during the construction of buildings

፱. በስህተት በፀደቀ ፕላን መሠረት የተገነባ ህንፃ በአዋጁ መሠረት እንዲስተካከል ትዕዛዝ ይሰጣል፤

9. Order the re-construction of building, built based on a plan which was approved mistakenly in accordance with this proclamation.

፲. አዋጁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰሩና አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንባቸው የተደረጉ ህንፃዎች እንዲመረመሩ የማድረግ እና ለህብረተሰቡ ደህንነት አስጊ ሆነው ከተገኙ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲፈርሱ ያደርጋል፤

፲፩. በህንፃ አዋጁ፣ በደንቡ እና በመመሪያው የተካተቱ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሆነው የተገኙ ግንባታዎች እንዲቆሙ፣ እንዲስ ተካከሉ ወይም እንዲፈርሱ ያደርጋል፤

፲፪. የአሰራር መመሪያ ማንዋሎችና ስታን ዳርዶች ያወጣል፤

፲፫. ለክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልግ መረጃ ዎችን ያደራጃል፤

፲፬. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## ፲. የህንፃ ሹሙ ሥልጣንና ተግባር

፩. የህንፃ ሹሙ የባለስልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ያስተባብራል፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ህንፃ ሹሙ፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተዘረዘሩትን የባለስልጣኑን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል፣ በትክክል ስለመ ተግበራቸውም ይከታተላል፣

ለ.በአዋጁና በደንቡ ላይ የተገለጹ ድንጋጌዎች በትክክል መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፣

10. Conducts investigation on building which built before coming into force of this proclamation and those excluded from the ambit of this law and order a re-construction or demolition of them if it is dangerous to the safety of the society.
11. Order stoppage; reconstruction or demolition of buildings which was found in contradiction with provisions of the building proclamation, regulation and directives.
12. Formulate work directives manuals and standards
13. Organize informations which are necessary for control and following up.
14. perform other activities in order to meet its objectives

## 10.Power and Duties of the building Officer

1. The building Officer shall co-ordinate, direct and manage the activities of building authority
2. With out prejudice the generality stated under sub Article (1) of this Article the building officer.

a. Exercise the power and duties specified under Article 9 and followup their proper implementation

ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ሐ. የባለስልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል።

መ. ለባለስልጣኑ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለስልጣኑን ይወክላል።

ረ. የባለስልጣኑን የሥራ አፈፃፀም እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቢሮው ያቀርባል።

ሰ. በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች ህግ መሠረት የባለስልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ያሰናብታል።

፫. የህንፃ ሹሙ ለባለስልጣኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፬. ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

b. Control the proper implementation of the provisions of the proclamation and regulation, order and take necessary measures.

c. Prepare the annual budget and program of the building authority and implement the same upon approval.

d. Effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the building authority.

e. Represent the building authority in its all dealings with third parties.

f. Prepare and submit the performance and financial reports of the building authority to the bureau.

g. Employee, administrator and dismiss employees of the building authority in accordance with the civil servant law of the Administration

3. The Building Officer may delegate parts of his power and duties to subordinate officials to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the building authority.

4. Perform other related activates assigned by the mayor.

## ፲፩.. <u>አገልግሎትን መግዛት</u>

፩. የህንፃ ሹሙ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመስራት የሚችል ባለሙያ የማይገኝ ሲሆን ይህንን ሥራ ሊሰራ ከሚችል የተመዘገበ

ባለሙያ ጋር አግባብ ባለው ህግ መሠረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተዋውሎ የሚያሰራው ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ፣ በደንቡ እና በውሉ መሠረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፣

፫. የህንፃ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተዋውሎ የሚያሰራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

## □ፍል ሶስት

## በጀት፣ የሂሳብ መዝግብና ምርመራ

### ፲፪. በጀት

የባለስልጣኑ በጀት በአስተዳደሩ የሚመደብ ይሆናል።

### ፲፫. ስለሂሳብ መዛግብት አያያዝ እና የበጀት ዓመት

፩. ባለስልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሠነዶችን ይይዛል።

፪. የባለስልጣኑ የበጀት ዓመት ከሐምሌ አንድ ቀን እስከ ሰኔ ሰላሳ ቀን ድረስ ይሆናል።

### 11. Buying of service

1. The building Officer shall enter into agreement with registered profession to carry out specific work when there is no professional profit for that particular work.
2. The professional who works based on the contract as per to sub Article (1) of this article shall have the responsibility to perform enline with this proclamation and regulation
3. The building Officer shall have the responsibility to ensure and follw up whether the professional who enter into contract and work as per sub Article (1) of this Article

## PART THREE

## Budget Books of account and Audit

### 12. Budget

The budget of the authority shall be allocated by the Administration

### 13. Record of books of account and fiscal year

1. The authority shall have full and reliable books of account and other financial documents.
2. The fiscal year of the authority shall commence on the 1st day of july and end on 30th day of june

### ፲፬. ስለሂሳብ ምርመራ

የባለስልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሠነዶች በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፭. ስለህንፃ ሹሙ

በአስተዳደሩ ከንቲባ የሚሾመው የህንፃ ሹም በአርክቴክቸር በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስት ራክሽን ቴክኖሎጂ እና በኮንስትራክሽን ማናጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ ልምድ ያለው መሆን አለበት።

ዝርዝር መመዘኛ መሥፈርቶች በአስተዳደሩ ካቢኔ ይወሰናሉ።

### ፲፮. ተጠያቂነት

፩. የህንፃ ሹሙ በአዋጁና በደንቡ ላይ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ባለመወጣት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በወንጀል ተጠያቂ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረትም ተጠያቂ ይሆናል፣

### 14. Audit

The books of account and money as well as property related documents shall be investigated annually by the chief auditor of the administration or other auditors assigned by the chief auditor general.

## PART FOUR
## Miscellaneous Provisions

### 15. The building Officer

The building Officer by the city mayor shall be graduated in artiicture, in civil engineering, construction technology and construction management or other related fields and relevant experiences in 1st degree.

particularities may be decide by the administration cabinet

### 16. Responsibility

1. Without prejudice the responsibility of building Officer specified under the proclamation, regulation he will be criminally liable for damages sustained by third parties because of fails his responsibility and also has civil liability as per the provisions of the civil code.

፪. የህንፃ ሹሙ የፈፀመው ጥፋት በፍትሐብሔር ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ጥፋት ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ያለ እንደሆነ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለደረሰው ጉዳት አስተዳደሩ በህግ መሠረት ተገቢውን ካሳ ከፍሎ አጥፊውን መልሶ ለመጠየቅ መብት አለው፣

## ፲፯. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

## ፲፰. መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላፍ

የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን የሚመለከቱ የመሬት ልማትና ማናጅመንት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለድሬዳዋ አስተዳደር የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ባለስልጣን ተላልፎአል።

## ፲፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩. የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊውን ደንብ ለማውጣት ይችላል።

፪. ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም የከንቲባው ጽህፈት ቤት አስፈላጊውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

If the foult of the building officer committed when he was performing his professional duty the administration sall pay compensation for the third parties and has the right to reclaim from the wrong doer.

## 17.Duty to co-operate

Every person shall have the duty to cooperate for the implementation of this proclamation.

## 18.Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations given to the Bureau of land development and management in relation to construction permit and control hereby transferred to the Dire Dawa construction permit and control authority.

## 19.Power to issue regulation and Directives

1. The cabinet of the administration may issue regulations for the implementation of this proclamation
2. The mayor’s office may issue directive for the implementation this proclamation and regulation issued there after

## ፳. ተ□ፃሚነት ስለማይኖራቸ□ ህጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪጻ □ጁም □ተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፩. <u>አ□□ □ሚናናበት ጊ□</u>**

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ □ታትሞ ከወጣበት ጊ□ □ምሮ □ናና ጁሆናል፡፡

**ትሬ□ዥ □ካቲት ፳፩ቀን ፳፻፮ □/ም**

**አሰድ ዚያድ**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

**20. <u>Inapplicable laws</u>**

No law, regulation, directive or particie may in so faras it is inconsistent with provisions of this proclamation, may be applicable with respect to matters provided for by this proclamation.

**21. <u>Effective date</u>**

This proclamation shall enter into force as of the date of its publication Dire Negarit Gazeta

**Dire Dawa Feb 28 Date of 2014**

**Assed Ziyad**

**Mayor of Dire Dawa Administration**